DENVER PUBLIC SCHOOLS | Student Equity and Opportunity
Success in School, Success in Life
780 Grant St., Denver, CO 80203
720-423-1416

ፌብሯሪ 24፣ 2017

ውድ የDPS ማህበረሰብ፤

በኮሎራዶ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ በርካታ የመፕስ /Mumps/ ቫይረስ ህመሞች ሪፖርት ተደርገዋል። በቫይረሱ መለከፍ የሚታዩ ምልክቶችን እንዲያውቁ እና ስርጭቱን ማስቆም የሚቻልባቸውን መንገዶች አስመልክቶ እንዲነቁና እንዲጠነቀቁ ሊያደርገዎ የሚችል መረጃ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል።

መፕስ /Mumps/ የሚተላለፈው በቫይረሱ በተለከፈ ሰው ሳል እና ንጥሻ ወይም እንደ ስኒዎች እና ማንኪያዎች ያሉ የምግብ ዕቃዎችን በመጋራት በሚከሰት የቀጥታ ምራቅ ንክኪ ነው። መፕስ /Mumps/ ሊዛመትባቸው የሚችሉ ቦታዎች እንደ አብያተ ክርስቲያን፣ ት/ቤቶች፣ የገቢያ ቦታዎች እና የመዝናኛ ማእከላት ያሉ ሕዝብ የሚበዛባቸው ማናቸውም ቦታዎች ሊሆኑ ይችላል። ስለዚህ ወደት/ቤት መምጣት ያለባቸው ከምልክቱ ነፃ የሆኑ ተማሪዎች ብቻ መሆናቸው ጠቃሚ ነው።

ተማሪዎች በሽታው እንዳይዛቸው የመከላከያ ተመራጩ መንገድ የMMR ክትባት እንዲወስዱ ማድረግ ነው። ክትባቱን በነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ የሚሰጡ ብዙ የአካባቢ ኤጀንሲዎች/ክሊኒኮች አሉ። እነዚህን ክሊኒኮች ወይም የልጅዎን የክትባት ሪኮርድ(ዶች) አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት የት/ቤቱን ነርስ ያነጋግሩ።

በት/ቤታችን ውስጥ ወረርሽኝ ስለመከሰቱ DPS መረጃ አልተሰጠውም፤ ስለዚህ እኛ ማኅበረሰብ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ዝቅተኛ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ከስቴት እና ከአካባቢ የሕዝብ ጤና ኤጀንሲዎች ጋር የቅርብ መረጃ ልውውጥ እናደርጋለን። ተጨማሪ መረጃ እንደደረሰንም ለእርስዎ እናሳውቅዎታለን።

እናመሰግናለን!

የተማሪ እኩልነት/ፍትሃዊነት እና ዕድሎች ጽ/ቤት